

# ደጉ ሳምራዊ

ይህን ታሪክ የተናገረው ኢየሱስ ሲሆን ታሪኩን የተናገረውም አንድ ሰው የዘላለምን ሕይወት እንዴት እንደሚያገኝ ሲጠይቀው ነበር።

“በሕግ የተጻፈው ምንድር ነው? እንዴትስ ታነባለህ?” ብሎ ጠየቀው።

ሰውዬውም መልሶ። “ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ኃይልህም በፍጹም አሳብህም ውደድ፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው።”

ሰውዬውም መልሶ “ባልንጀራዬስ ማን ነው?” ብሎ ኢየሱስን እንደገና ጠየቀው።

ከዚያም ኢየሱስ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ሲጓዝ ስለነበረና በወንበዴወችና በዘራፊዎች ተዘርፎና ተደብደቦ መንገድ ዳር ላይ በሞትና በሕይወት መካከል ስለተተወ አንድ ሰው ታሪክ ይነግረዋል።
ሰውዬው በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳለም አንደ ካህን በዚያ አለፈ። ቁስለኛውን ሰውዬ ቢያየውም እንኳን እንዳላየ አቅጣጫውን ቀይሮ ሄደ። ቀጥሎም ሌዋዊ መጣ። እሱም ተስፋ የሌለውን ሰው ተመልክቶ ከመርዳት ይልቅ አቅጣጫ ቀይሮ እንዳላየ ሆኖ ሰውዬውን ሳይረዳው ሄደ።

ቀጥሎም አንድ ሳምራዊ መጣ። ለተጎዳው ሰው የሚችለውን እንክብካቤ ካደረገለት በኋላ በገዛ አህያው ጭኖ ማረፊያ ተከራየለት። ሳምራዊው ማንኛውንም ወጪ ሁሉ ከፈለለት።

ኢየሱስ ታሪኩን ከጨረሰ በኋላ ሰውዬውን “ ከእነዚህ ሶስት ሰዎች ለተጎዳው ሰው እውነተኛ ባልንጀራ ማነው?” ብሎ ጠየቀው።

ሰውዬውም “ለተጎዳው ሰው ያዘነለትና የተንከባከበው ነዋ!”
ኢየሱስም “አንተም ሂድና እንዲሁ አድርግ አለው።

*የደጉ ሳምራዊ ታሪክ በአዲስ ኪዳን በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 10፡ 25 – 37 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ይገኛል።*

http://gardenofpraise.com